# ኢ.ዴፓ የአጭር ጊዜ የስራ ዕቅድ አወጣ

ጥር 24 ቀን 2001 ዓ.ም በተካሄደው የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢ.ዴፓ) 4ኛ ድርጅታዊ ጠቅላላ ጉባዔ የተመረጠው የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ፤ ጠቅላላ ጉባዔው በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ያስቀመጣቸውን የፓርቲውን የወደፊት የትግል አቅጣጫ የሚያመለክቱ ግቦች እውን ለማድረግ ቅድመ ዝግጅቱን አጠናቀቀ።

በዚህ መሠረት፣ ከመጋቢት ወር 2001 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ባለው ጊዜ የፓርቲው ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ የሆኑ ሁለት ዋና ዋና ተግባራትን ማለትም፤ "የፓርቲውን ድርጅታዊ መዋቅር ማጠናከር እና የፓርቲውን የ3ኛ አማራጭነት ሚናና አስተሳሰብ በሕብረተሰቡ ውስጥ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችሉ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን ለማዘጋጀት" የአጭር ጊዜ ዕቅድ አዘጋጅቷል።

የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ መዋቅሮችን፣ አመራር አካላትንና በፓርቲው ከፍተኛ አመራር መዋቅር ስር በሚገኙ ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች የሚታቀፉ የቋሚ ኮሚቴ አባላትን መርጦ መድቧል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ በክልል ደረጃ ስድስት አስተባባሪ ኮሚቴዎች የተዋቀሩ ሲሆን፤ በሰው ኃይል አደረጃጀትም ከስራ አስፈፃሚ፣ ከተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ ከክልል ምክር ቤት አባላትና ከየክልሉ የተወጣጡ እንዲሆን ተደርጓል። የኮሚቴዎቹ ዝርዝር አፈፃፀም መመሪያም በስራ አፈፃሚ ኮሚቴው ተዘጋጅቷል።

በሌላ በኩል፤ "የፓርቲውን የ3ኛ አማራጭነት ሚናና አስተሳሰብ በሕብረተሰቡ ውስጥ ግንዛቤ ለመፍጠር" በአዲስ አበባ፣ በባህር ዳር፣ በመቀሌ፣ በድሬዳዋና በአዋሳ ከተሞች ህዝባዊ የውይይት መድረኮችን ለማዘጋጀት ዕቅድ ተይዟል። በነዚህ መድረኮችም አማካይነት ከፓርቲው አባላትና ከደጋፊዎች ጋር በወቅታዊ የሀገሪቱ የፖለቲካ ጉዳዮች፣ በፓርቲው የወደፊት የትግል አቅጣጫና ፓርቲው ስለሚከተለው "የ3ኛ አማራጭ" አስተሳሰብና መሠረታዊ መርሆዎች ላይ በወጣው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ውይይቱ ይካሄዳል። ለነዚህ የውይይት መድረኮች አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች የተለዩ ሲሆን፤ በአስተባባሪ ኮሚቴዎችና በአባላት ተሳትፎ ተፈፃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

**(በኢ.ዴፓ የሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ የተዘጋጀ)**